# የፍትህ ዘርፉ ተግዳራቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች!

ክፍል አንድ

ተስፋዬ ለማ

ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ፈርጀ ብዙ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት ቀላል አልሆነም። ዘርፉ ለበርካታ ዓመታት የነበሩበትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት መጓተት ታይቶበታል። እነዚህ ለዘመናት የዘለቁ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ተግዳራቶችን ለመሻገር አሁንም ጥረቱ ቀጥሏል። የፍትህ ማሻሻያ ተነድፎ ሥራ ላይ ውሏል። ማሻሻያው በዘርፉ የሚታዩ መሠረታዊ ማነቆዎችን በመለየት ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ፍትህንና መልካም አስተዳደርን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻለው ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ሕብረተሰቡ በየደረጃው ተጠቃሚ መሆን ሲችል ነው። ሕዝቦቿን መመገብ ያልቻለችና በድህነት የተዘፈቀች አገር ፍትሃዊነትና መልካም አስተዳደርን ማስፈን አትችልም። ዜጎች ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፣ ፍትሃዊ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማግኘት፣ ተመጣጣኝ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ መሆን ካልቻሉ መልካም አስተዳር እውን ሆኗል ማለት ያዳግታል።

ልማትን ማረጋገጥ ለፍትህና መልካም አስተዳደር መረጋገጥ የበኩሉ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ሁሉ ፍትህንና መልካም አስተዳደርን እያረጋገጡ መሄድም ለልማቱ መፋጠን ቀላል የማይባል አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋል። ሁለቱ ዐበይት ነገሮች እርስ በርሳቸው ተመጋጋቢ ናቸው። ሰፊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴ ማዕከል በሆነችው ኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረታታ ነው። ፍትህንና መልካም አስተዳደርን በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚያስችል መሠረት እየገነባ የመጣ ቢሆንም በፍትህ ዘርፍ ያሉትን ችግሮች መፍታት አልተቻለም።

የፍትህ ሴክተሩ በአገሪቱ ልማት የሚኖረውን በጎ ሚና እንዲወጣ በማድረግ ረገድ እጥረት ታይቷል። በዚህ የተነሳ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ዘርፉ ያበረከተው አስተዋጽኦ የቀጨጨ ነበር ማለት ይቻላል።

በአገራችን ያለው የፍትህና የመልካም አስተዳደር ችግር ከተሳሳተ አመለካከት እንደሚጀምር የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህ የአመለካከት ችግር የአገልጋይነት ሚናን የመቀበልና ያለመቀበልን ያመለክታል። የመንግሥት ሹመኛውም ሆነ ሲቪል ሰርቫንቱ የአገልጋይነት መንፈስ በአዕምሯቸው ማስረጽ አልተቻለም።

የህዝብ አገልጋይ እንጂ ተገልጋይ አንዳልሆነ አምኖ የመቀበል ችግር እስካሁን ድረስ መቅረፍ አልተቻለም። ከህዝብ ጋር የዕለት ተለት የቅርብ ግንኙነት ያለው አመራርና ሠራተኛ በእምነት ይዞ ሊተገብረው ባለመቻሉ በቀደሙት ሥርዓታት የነበረው የተገልጋይነት መንፈስ ማስወገድ አለመቻሉን ያሳያል። ይህ ዋናው ማነቆ ነው።

የእውቀትና የክህሎት ችግር በባለሙያዎች መኖሩ ደግሞ ሌላው ማነቆ ሆኖ ተለይቷል። ከዚያም አልፎ የአመለካከትና የሥነ ምግባር ግድፈት ይታያል። በፈጻሚዎች የሚታየው የመልካም አስተዳደር ችግር እስከ ኪራይ ሰብሳቢነት የሚደርስ እንደሆነም የተለያዩ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ።

መንግሥት "በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት" የሚለውን መሪ ሀሳብ በመያዝ የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ ጽኑ እምነት በመነሳትም በአገር አቀፍ የፍትህ ሴክተር ያለውን የፍትህና የመልካም አስተዳር ሁኔታ በጥናት በመፈተሽ የማሻሻያ ፓኬጅ በመንደፍ ወደ ትግበራ ተገብቷል።

ይህ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የፍትህና መልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ባለፈው ወር ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በተካሄደው ስብሰባ ተገምግሟል። የፍትህና የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ አተገባበር፣ የተገኙ ለውጦችና ያጋጠሙ ማነቆዎች ተጠንተው ለውይይት ቀርበዋል።

የልማት ስኬት ከመልካም አስተዳደርና ከፍትህ ውጭ የማይታሰብ በመሆኑ ሁለቱ ተናበው መፈፀም እንዳለባቸው በመታመኑ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጁ ተነድፎ ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም  የፍትህ ተቋማት ለበርካታ ዓመታት በበርካታ ችግሮች የተሸበቡ በመሆናቸው በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ፈታኝ መሆኑን ነው  ጥናታዊ ሪፖርት የጠቆመው።

ሌላ መሠረታዊ ማነቆ  ግልጽነትንና ተጠያቂነት አለመኖር  ነው። የሚወጡ ሕጎች፣ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ለማድረግ የሚያስችል አሠራር አልተዘረጋም።  በየደረጃው ያለው አመራርም ችግሮቹን ለይቶ ከሕዝብ ጋር ፊት ለፊት ተወያይቶ ለማስተካከል የቁርጠኝነት ማነስ ተስተውሏል።

የፍትህና መልካም አስተዳደር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ቢኖርም በአሠራሮች ላይ ግልጽነት ካልሰፈነ የተፈለገውን ያህል ውጤት ሊመጣ አይችልም። አቤቱታ አቀራረብ፣ የክስ አመሠራረት፣ በምርመራ፣ በኤግዚቢት አያያዝ፣ በክርክርና በውሣኔ አሰጣጥ ዙሪያ  ሕዝቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው አልተደረገም።

በአንዳንድ የፍትህ ተቋማት እንደሚታየው ግልጽነትን ባጅና የመለያ ምልክቶችን ማንጠልጠል ብቻ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ አለ። በእርግጥ ይህ ተገልጋዮች የት መሄድ እንዳለባቸውና ከማን ጋር እየተነጋገሩ እንዳሉ ለማወቅ እድል ይፈጥርላቸዋል። ሆኖም ግን ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት መብታቸው እንደሆነ ተገንዝበው ለመጠየቅ የሚያስችላቸው አይሆንም።

የፍትህ ሴክተሩ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ማቀፍና መተግበር እንደሚኖርበት የአደባባይ ሚስጢር ነው።  ግልጽነት፣ አሳታፊነትና ተጠያቂነትን ማዕከል ያደረገ አሠራር በዘርፉ መዘርጋትና መተግበር ይኖርበታል። የፍትህ አካላት ፍትህን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

የፍትህ አስፈጻሚው ፍትህን ሲያዛባ ደግሞ በሕጉ መሠረት ተጠያቂ የሚሆንበትን አሰራር መዘርጋትና መተግበር የግድ ይገባል። ተጠያቂነት መሠረታዊ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው። ተጠያቂነትን መሠረት አድረጎ የሚደረግ እንቅስቃሴ ህዝቡ በሥርዓቱና በመንግሥት ላይ እምነት እንዲኖረው ያግዛል።

የዘርፉ ለኪራይ ሰብሳቢነት ተጋለጭነት ሌላው መሠረታዊ ማነቆም ነው። በክስ አመሠራረት፣ በሕግ አተረጓጎም፡ በመዝገብ አዘጋገብና በሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ትውውቅን፥ ዝምድናንና ጥቅምን መሠረት ያደረገ አድሎአዊ አፈጻጸም መኖሩ ነው።

ሕዝቡ አንዱ ባለድርሻ የመሆኑን ያህል በእቅድና በአፈጻጸምና በግምገማ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል። በቅርብ ጊዜ እየታየ ከመጣው መሻሻል በስተቀር ባለፉት ዓመታት እቅዶች ሲወጡ ህዝቡ ተወያይቶ አያፀድቃቸውም። አፈጻጸማቸው በምን ደረጃ እንደሆነ ለመረዳትም በግምገማ እንዲሳተፍ የሚደረግበት አሠራር ስላልነበረ ችግሮችን በመለየትና የአፈታት ስልታቸውን በሚመለከት ከሕብረተሰቡ ተገቢ ግብዓት አይሰበሰብም።

በመሆኑም ህዝቡ የፍትህ ሴክተሩ ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች የሚያውቀው ነገር የለም። በአፈጻጸማቸው ስለሚታዩ ችግሮች ከእለት ተለት እንቅሰቃሴው ጋር ተያይዞ ከሚያጋጥመውና ከሚያየው ብልሹ አሠራርና የፍትህ መጓደል እየተነሳ እሮሮ ያሰማል።

የችግሮቹ ባለቤት መንግሥትን ብቻ አድርጎ ይወስዳል። ለችግሩ የራሱ ድርሻ እንዳለበት አይገነዘብም። በዚህ መልክ ሕዝቡም ለፍትህ ሥርዓቱ መሻሻል ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ ማበርከት አልቻለም። የድርሻውን ማበርከት እንዳለበትም በውል የተገነዘበበት ሁኔታ እንደሌለ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ካልተረጋገጠ የማሻሻያ ባኬጁን በአጭር ጊዜ ተግብሮ እምርታ ማምጣት አይቻልም። ይህ ስኬታማ የሚሆነው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ ጨብጠው በቅንጅት ከሰሩ ነው። የፖለቲካ ፍላጐትና ቁርጠኝነት በመኖሩ ብቻ ፍትሕና መልካም አስተዳደር ይሰፍናል ተብሎ አይታሰብም። ስኬት የሚገኘው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከአመራሩና ከባለሙያው ጋር ቅንጅት ፈጥረው ሲሰሩ ነው። ይህንን ለማድረግ ጥረት ቢደረግም አጥጋቢ ውጤት ማግኘት አለመቻሉን የቀረበው ጥናታዊ ሪፖርት አመላክቷል።

ወንጀልን ለመከላከል በጥናት ላይ የተመሠረተ ስትራቴጅ አለመነደፉም ሌላው የመልካም አስተዳደር ማነቆ ሆኗል። የህብረተሰቡ ለወንጀል ተጋላጭነት ሥጋት በሚፈለገው መልክ አልቀነሰም።

የቅንጅት ጉድለት ሌላው ለዘርፉ ስኬት መሰናክል ነው። በሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ያለው ተቀራርቦና በቅንጅት የመሥራት ባህል በደንብ ያደገ አይደለም። የሚታዩ አንዳንድ መልካም ጅምሮች ቢኖሩም የተዋጣለት ቅንጅታዊ አሠራር አለ ማለት አያስችልም።

ፌዴራል ከክልል ጋር ተቀራርቦ እየተናበቡ ለመስራት የሚደረገው ጥረትም ጠንካራ የሚባል አይደለም። በአገር አቀፍ ደረጃ ግልጽ የሆነ የሥራ ግንኙነትና የኃላፊነት ወሰን በማያሻማ መንገድ ተቀምጧል። ይህንን በመተግበር የሚታዩ ጉድለቶች ለፍትህ ዘርፉ ስኬት ጫና ማሳደሩ አይቀሬ ይሆናል።

ሕዝቡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ አለማግኘቱም ሌላው የፍትህ ዘርፉ የመልካም አስተዳደር ችግር መገለጫ ሆኖ ተለይቷል። በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ሕዝብን በክብር አለማስተናገድም እንዲሁ። የአገልጋይነት ስሜት አለመኖር፣ ውሣኔን በጽሑፍ አለመግለጽ፣ የተገልጋዮች ምልልስ ማብዛትና ወዘተ ይስተዋላሉ። በሥርዓት የተዘረጉ የአገልግሎት አሰጣጥና የቅሬታ ማስተናገጃ ማዕቀፎች አለመኖራቸውም ሌላው ችግር ነው።

ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ለመሻገር መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። መልካም አስተዳደር የሕግ የበላይነትን ማዕከል አድርጎ ከብልሹ

አሠራርና ከሙስና በፀዳ መልኩ ሕዝብን ማገልገል በመሆኑ መንግሥት ይህንን የሕዝቦች መብት የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በመረዳት መጠነ ሰፊ ንቅናቄ በመፍጠር ላይ ይገኛል። ችግሮች ይኑሩ እንጂ ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እስካሁን በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ቀላል የማይባሉ መሻሻሎችም ታይተዋል። ሆኖም ግን ችግሩ ለዘመናት ሥር ሰዶ የቆየ በመሆኑ በቀላሉ ሊስተካከል እንደማይችል በመገንዘብ የማሻሻያ ፓኬጅን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

መንግሥት እያደረገ ባለው መጠነ ሰፊ ዘመቻ የፍትህ ሴክተሩን ተግዳራቶች ለመፍታትና በመልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ያስችላል የሚል እምነት ተይዟል። በጠቅላይ ሚኒስቴር አዳራሽ በተካሄደው ሃገራዊ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መድረክ ላይ እንደተገለጸው መንግሥት ከኅብረተሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነትን በመፍጠር በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ዝግጁነቱን እየገለፀ ይገኛል።

ይህ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መድረክ ከቀደሙ ሌሎች መድረኮች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው በዘርፉ የታዩ ችግሮችን ነቅሶ ያወጣ መሆኑ ነው። ከአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ጠንካራ ጎኖቹ በንጽጽር ለምን እንዳልቀረቡ የተነሳ ሲሆን በዋናነት መስተካከል በሚገባው ነገር ላይ ውይይቱን ማድረጉ ለቀጣይ ችግሩን ለመፍታት ያስችላል በሚል እሳቤ እንደሆነ ተገልጿል።

በተቀመጡት የፍትህና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመወያየት ዘርፉ በሥነ ምግባር መርሆች ተቃኝቶ የሚጓዝበትን መንገድ ለማመቻቸትና የችግሮቹን ምንጮች ለማድረቅ ከሚል መነሻ ሪፖርቱ በተለየ መልኩ ሊቀርብ ችሏል። የቅሬታ አቀባበልንና የምላሽ ሰጪነት አሠራር ሥርዓትን በመዘርጋት፣ የዜጎች ቻርተርን በመቅረጽና በማስፈጸም፣ የአመለካከት መቃኛ መድረኮችን በመፍጠር ተግዳራቶቹን ለማስወገድ እየተሰራ እንደነበርና አሁንም በቀጣይ እቅድ ልዩ ትኩረትን አግኝቶ የሚሰራበት ይሆናል።

በምክክር መድረኩ ላይ የሕዝብ ተወካዮች፥ የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፥ ባለሀብቶች፣ የሕዝብና የሙያ አደረጃጀቶች ተወካዮችና ከፍትህ ሴክተሩ የተወከሉ አካላት ተሳትፈዋል።

ተሳታፊዎቹ እንደገለጹት የቀረቡት ችግሮች ትክክለኛ የሕዝቡ ጥያቄዎች ናቸው። ሕዝቡ በሕጎች ላይ ግልጽ ግንዛቤ እንዲይዝ አይደረግም። በእቅድ አወጣጥም ሕዝቡ አይሳተፍም። በታችኛው አመራርና በፈጻሚው በኩል የስብሰባ መብዛት ይታያል። ይህም ፈጣን ምላሽ እንዳይሰጥ አድርጓል። የመረጃ ክፍተትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና እንግልቶችም እንደሚስተዋሉ ነው የተገለጸው። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍም የተለያዩ የሕዝብ አደረጃጀቶችን መጠቀም ሁነኛው መሣሪያ መሆኑንም ያሰምሩበታል።

የፍትህና የመልካም አስተዳደር ክፍተት ጥናታዊ ሪፖርት በዓይነቱ ልዩ እንደሆነ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። ሴክተሩ ከዚህ ቀደም ይቀርብ ከነበረው የሪፖርት አቀራረብ የተለየና ለሌሎች ተቋማት አርአያ ሊሆን የሚገባው እንደሆነ ተገልጿል። ችግሮቹን በተገቢው መንገድ መለየቱ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ በር ከፋች እንደሆነም ተጠቁሟል።

ህዝቡ ያለምንም ዓይነት ልዩነት በእኩልነት በልማታዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ውሣኔ በመስጠት ሂደት መሳተፍና ከዚህም በእኩል ተጠቃሚ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዜጎች አቅም በፈቀደ መጠን በቂና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት፣ የሥራ ዕድል፣ የጤና አገልግሎት፣ መሬት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውኃና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን በፍትሃዊነትና ግልጽ በሆነ አሠራር የማግኘት መብታቸው ሊረጋገጥ ይገባል። መንግሥት እያከናወነ ያለው ጥረትም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች በግልጽ በሚታወቅ ፖሊሲና አሠራር የሚቀርቡ፣ ሁሉንም አካባቢዎችና የኅብረተሰብ ክፍል በእኩልነትና የሚያገለግሉና በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ አግባብ በአገሪቱ የሚመዘገበው ልማትና የሚደረግ ማንኛውም የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊ ከሆነ የሚኖረውን ልማት

ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግና መልካም አስተዳደርንም ለማስፈን የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ሴክተሩ በዚህ ረገድም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ተብሏል።

ፍትህና መልካም አስተዳደር ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚጠናከረውና ለቀጣይነቱ ዋስትና የሚያገኘው አሳታፊና ፍትሐዊ የሆነ ፈጣን ልማት በማምጣት ብቻ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ፈጣን፣ ፍትሐዊና ቀጣይ ልማትን ለማረጋገጥ መልካም አስተዳደር ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ እንዳለው ይታወቃል።

ስለሆነም ፍትሃዊ ልማትና መልካም አስተዳደርን አስተሳስሮ ማስኬድ ብቸኛው የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መንገድ በመሆኑ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት መልካም አስተዳደርን ከልማት ጋር አስተሳስሮ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ማቅረብ ሌላ ለፍትህና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ወሣኝ ነው።

የተለያዩ አገልግሎቶች፣ የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለነዋሪዎች የሚቀርቡበትን የአሠራር ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን መርህ በተግባር ለመተርጎም የአገልግሎት ሰጭና ተቀባይ መብትና ግዴታን በግልጽ መለየትና ማሳወቅና ሥራዎቹን ለመፈፀም የሚያስችል የአደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም መፍጠርን፣ አማራጭና ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን መጠቀም ማዕከል ያደረ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡

የማሻሻያ ፓኬጁን ከልማት እቅድ ጋር ለማስተሳሰር በተደረገው ጥረት ካሁን በፊት ከነበረው የታየው መሻሻል ቀላል ግምት የሚሰጠው ባይሆንም የተፈለገውን ያህል መጓዝ አለመቻሉ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የፍትህ ሴክተሩ ቀልጣፋና ፍትሀዊ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው አደረጃጀት አለመፍጠሩ ሌላው የዘርፉ ማነቆ ነው።

ፍትህና መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ ከተቻለ ሕዝቡ በምክንያት የተመሠረተ ድጋፍና ተሳትፎ ለማድረግ እድል ይኖረዋል። ከዚህም ባሻገር ለዴሞክራሲ

ሥርዓት መጠናከር፣ ለአስተማማኝ ሠላም መስፈን እንዲሁም ለህግ የበላይነት መረጋገጥ አዎንታዊ ተራ ይኖረዋል።

ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ አመራሮችን ሙያተኞችን አቅም በቀጣይነት ማሳደግ፤ ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶችና ስለሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች ግልጽ ግቦችን ማስቀመጥ፤ ለህዝቡም በየደረጃው ግልጽ ማድረግ ያሻል።

በዚህ መልክ ችግሮቹ ከተዳሰሱና በምን መልክ መፈታት እንዳለባቸው መግባቢያ ላይ ከተደረሰ በኋላ የቀጣይ እቅድ ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል። እቅዱ ያቀፋቸው ዋና ዋና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በሚመለከት ደግሞ በቀጣይ ክፍል ይቀርባል።